# <u>አፍ ሲያመልጥ-- የፈገግታ ፖለቲካ</u>

ሀማ ቱማ

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታ በከተሜዎቹ አነጋገር ቀፋፊ ነው:: የፖለቲካ መሪዎችም በአብዛኛ ው-- እንዲሁ በከተሜዎቹ አነጋገር-- ደባሪ ናቸው:: ችግሩ የዕድሜ ብቻ አይደለም:: በአንፃራዊ ዕይታ ወጣት የተባሉትም ከደባሪ አልፎ ከሀዲ ተለጣፊ እየሆኑ ስላስቸገሩ አልፎ አልፎ ፈገግ የሚያሰኙ ብቅ ሲሉ እንደ አረቦቹ ሹክረን ወይም ዕድሜ ለወያኔ መሬታቸው ለሻዕቢያ እንደተሰ ጠባቸው ሳሆዎች/አዲ ኢሮቦች/ ዮሖምሲሴ (ይ) ማለታችን አልቀረም:: ለመራቀቅ ብዬ እንጂ ( እንደ ሰፈነው የጥራዝ ነጠቆች እንግሊዝ ከአፌ አልጠፋ አለኝ ፈሊጥ) ነገሩ አመሰግናለሁ ማለት ነው በሀሉቱም::

ወደ 1997 ዓመት ገደማ በረከት ስምዖን የተባለው ፎርጅድ/አስመሳይ/ አማራ ሲናገር ተቃዋሚዎ ች በምርጫ የቀናቸው በነፋስ ተረድተው ነው ብሎ አስቆን ነበር:: የሀገራችን ነፋስ ሳይቀር ፀረ ወያኔ ሆኖ የሕዝቡን የምርጫ ወረቀት ከወያኔ ኢሕአዴግ ሳጥን እያወጣ ወደ ቅንጅትና ህብረት ሳጥኖች ሲከት ታየንና ሳቅን:: በቀን ሶስቴ ትበላላቸሁ ብሎ ቀን ሙሉ ያስራበን አገዛዝ ሳቅ ነስቶን ቆይቷልና በሰውየው ንግግር ተደሰትን:: ሳቅና ደስታ እንደ ምግብና ሰላም የጠፋባት ሀገር ናትናም በዚችው ደስታ ረካን:: ቀደም ሲሉ በረከትና አለቃው አንድም የፖለቲካ እስረኛ የለንም ሲሉ በምፀት ፈገግ ያስደረጉንን ትቼ ማለት ነው:: በዚያው ወቅት አንድ አዛውንት የፖለ ቲካ መሪ ደግሞ ለአዲስ አበባ ሕዝብ ምን ይመኙለታል ቢባሉ ከሁሉም በፊት እንደ አውሮጳ ዓይነት ትራም ካር/ የኤሌክትሪክ ባቡር/ ማለታቸውም አስፈንድቆን ነበር:: በተለይ በዚያን ጊዜ ም ኮረንቲ በፈረቃ ያውም በቁጠባ የሚለው መፈክር በሕዘብ ላይ ይጮህ ነበርና:: የፖለቲካ መሪ ዎች ብዙ ጊዜ ከተጨባጭ ሁኔታው ርቀው በአየር ላይ ይንሳፈፋሉ የሚባለው ከእውነት የራቀ አይደለም:: በዚያው ሰሞንም ሌላ የፖለቲካ መሪ--ጠንክሮ ከመታገል ልምጥ ልፍስፍስ ማለቱ የሚቀናው ዶክተር ደግሞ-- የሀገሪቷ ፕሬዚዳንት ለመሆን ሊወዳደር ተነሳና ሲወድቅ በዚች ሀገር ዴሞክራሲ እውነትም የለም ብሎ አሳቀን:: ቀደም ሲለ ሌላ የዚሁ ዶክተር መሰል ሰው ለእራት የጋበዛቸው ጓደኞቹን ፖሊስ ቢያሳደድበት ተመሳሳይ ተዓምር ተገልጦለት ለካስ በዚች ሀገር ዴሞክራሲ የለም ብሎ አስቆን ነበር:: ለፕሬዚዳንትነት የተወዳደረው ቢያሸንፍ ኖሮሳ? ዴሞክራሲው ሞልቶ ፈሰሰ ሊባል! የወያኔአገዛዝ ፕሬዚዳንት በወያኔ መሰየሙን ያላወቀ ተቃዋሚ ወይም ፖለቲከኛ አያስቅም! ከዚያም መለስ ዜናዊ የተባለው ቁጥር አንድ ደባሪ ደግሞ ምን እንደነካው ሳይገልፅ የሶማሊያን ድንበር ተሻገርን እንጂ ሶማሊያን አልወረርንም ብሎ ሳቅ በሳቅ አደረገን:: ተፎካካሪው ሚስቱ አዜብ ደግሞ ልጆቿን ለማስተማር ገንዘብ እንዴት እንደሚያጥራ ት ስትገልፅ ስንሰማና ስናይ ፀረ ሕዝቡን ወያኔ ልናመሰግን ትንሽ ቀረን:: ቢርበንም አሳቁን!

ታዲያ የወያኔ ባልት በየቀኑ አይደለም፡፡ በየአምስት ዓመቱ ምርጫ ብሎ ብቻ እየመጣ አስችግሯል፡፡ በመሀሉ ድብርት ከረሀብና ከወያኔ ጥይት ቀድሞ ሊገለን ሲል አንዳንዶች ያዝኑና ለፈገግታ ያህል ፖለቲካ እየተናገሩ ይረዱናል፡፡ ለምሳሌ ሰሞኑን በኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ መኪና ተሰራ የሚለው ዜና ቢያንስ አዲስ አበባዎችን በሳቅ ሲገድል ከረመ ተብሏል፡፡ ሳሊኒ ኩባንያ ጉቦ ሰጥቶ አለጨረታ አሸንፎ ሰራሁ ያለው ግልገል ጊቤ ግድብ በተመረቀ በአስር ቀኑ ትልቁ ቦዩ ሲፈርስ ኮረንቲ በዋናይቱ መዲና ጠፍቶ ሰውም ፋብሪካም እየተሰቃዩ መሆናቸውን ራሱ በወያኔ ሳይቀር እየተናገረ ባለበት በኮረንቲ የሚሰራ መኪና ፋብሪካ ስራ ጀመረ መባሉ መቸም የቀልድ ቀልድ መሆኑ አልቀረም ፡፡ ያልሳቀ የለም፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ ደግሞ ያ የለመደበት ዶክተር ተቃዋሚ በሉኝ ባይደግሞ አልሳቁም ብሎ አዘነልን መሰል ዓላማችን የሚቀጥለው ገዢ ፓርቲ ለመሆን ነው ብሎ አንከተከተን፡፡ የእሱ ድርጅት ገዢ ፓርቲ ቢሆን ካለው አገዛዝ በምን ይለያል የሚለውን ወደ ጎንእንኳን ብንተው በመጪው ምርጫ ሲያሸንፍ የሚታየው ተላላ መሆኑ ቢያሳዝንም ማሳቁ አልቀረም፡፡ ይህን ዓይነት ቀልደኞችና ህልመኞች መሪህ ነን የሚሉት ሕዝብ በጣም የታደለና ሁሌም የሚጨቆን መሆኑ መቸም የሚሳት አይደለም፡፡ የመርካቶ አራዳ ዘያሪዎች መርቅነው ብን ሲሉ የሚደልቁትን ያስታውሳል፤

*" እነዚህ ቃፊሮች ምንኛ ተጎዱ*
*አላህ ሞተ ብለው ሁሌ የሚርዱ*
*አላህ መቼ ሞተ መቼ ተቀበረ*
*ሰማይና መሬት በማን እጅ አደረ!"*

መለስ ዜናዊ መቼ ሞተና ነው እነ ዶክተር ምርጫ አሸንፈው ገዢ ፓርቲ የሚሆኑት? ለነገሩ ያው ገዢነት ነው በዚህም በዚያም እንጂ ሕዝብን ማገልገል ከቶም አይጠቀስም፡፡ የአብዛኛዎቹ ዓላማ መግዛትና በዚያውም መክበር ነውና፡፡ የምርጫው ውጤት ገና አልታወቀም እየተባለ ሲቀለድና (አንዳንድ የጨው ተራራ ሲናድ የሚስቁ ሞኞች ደግሞ አዎና ሲሉ) መለስ ዜናዊ ደግሞ የምን ቀልድ ብሎ " ከምርጫው በኃላ በምርጫው ወቅት መስመር የሳቱተን ለፍርድ እናቀርባለን" ብሎ ከወዲሁ አሸናፊ ማን እንደሆነ የተናገረውም ፈገግ አሰኝቶናል፡፡ ነጋ ጠባ ሳቅ ፈላጊዎች ደግሞ ወያኔን የሚደግፉ ድረ ገፆች ጋ ሄደው የሚፃፈውን ቢያነቡ ከሳቅ ሌላ ምንም ስራ አይሰሩም ማለት ይቻላል፡፡ በተደረገው የድርጅቶች ክርክር ለምሳሌ ወያኔ ኢሕአዴግ ተቃዋሚዎችን ሲያስከነዳ እንደቆየ እመኑ የሚሉንም አሉ፡፡ መለስ ዜናዊም በስተርጅና ደበበ እሸቱን ሊሆን በመከጀል (የዱሮውን ደበበ ማለቴ ነው እነጂ ከርቸሌን ያደነቀውን ፖለቲካቅሮ አይደለም) ወይዘሪት ብርቱካን በቃሊቲ ደልቷት ወፈረች ብሎ ለመቀለድ ሞክሯል፡፡ በደስታ ባያስቀንም በትዝብት ፈገግ ማለታችን አልቀረም፡፡ በዚሁ ዓይነት በመቀጠል ወያኔ ለምርጫ ብዙ ሴቶችን በዕጩነት የማቀርበው እኔ ብቻ ነኝ፤ለሴቶች መብት ቆሜያለሁ ብሎ በይፋ ሲለፍፍ ሴቶ ች ብቻ ሳይሆኑ ወንዶችም መሳቅ ተገደናል፡፡

የዘመኑ የፖለቲካ መሪዎች የራሳቸው ሳይሆን የሌላውን ህይወት ለሀገራቸውና ለግባቸው መስዋዕ ት የሚያደርጉ ናቸው ተብሏል። የስልጡን ፖለቲካ አንድ ገፅታ ሳይሆን አልቀረም። ሌለውን ለሞት መጋበዝ ። ለሁሉም ችግር ምላሻቸው ባዶ ቃል ነውናም መርህና ሀቀኝነት የሚጠበቅባቸ ው አልሆኑም። እስከሆነም ከሚደብሩን ቢያስቁን ይመረጣል። አንዳንዶች ከመነሻው አራት ራሳ ቸውን ድርጅት ብለው በዚሁ ቁጥር ፀንተው ሲቆዩና ሲከርሙ ብንስቅ ሊፈረድብን አይገባም። የቁጥርን ነገር ወንድም ገሞራው ዜሮ ፊታውራሪ ብሎ ጨርሶታል። ወያኔ ለሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለቁጥር አህዝ ግድ የለውምና ለምርጫ የተመዘገበው ቁጥር ሲያንስ በራሱ ስልጣን 29 ሚሊዮኑን መዝግቦታል። ጅብ የቁርበትን ነገር ለእኔ ተዉት አለ ይባል የለ? ወያኔ ግን ዝናብና ድሎትን አመጣሁላችሁ እያለን እየፎከረ ለድርቁ ተጠያቂ ነህ ስንለው ማኩረፍ ባልተገባው ነበር። ወርቅ ዜጋ ፤ክልል አንድ ካለንም በኃላ ልዩነት ታደርጋለህ ስንለው ባልካደም ነበር። ግን ጭፍን ብሎና ሽምጥጥ አድርጎ ሲክድ ያስቀናልና ይቀጥልበት ማለቱ አስፈላጊ ነው። ልቀይር ካለም ከደደቢት ጀምሮ ያደቆነው ጂኒ ሊጣላውና ሊጎዳው ይችላልና ችግሩም ይገባናል። የአልጄርሱ ስምምነትና የዓለም ፍርድ ቤት ውሳኔ ድል ነው ብሎ ሲያስቀን እንደነበርም ማስታወስ ደግ ነው። መለስ ዜናዊ ከበለፀጉ ሀገሮች መሪዎች ጎን ፎቶ ሲነሳ አጆህ ብለው የሚያዳንቁት አትሳቁበት ቢሉንም መሳቅ ግን መቀጠላችን አይቀርም። እሬት በማር ዓይነት ፖለቲካው ከፈገግታ ጋር ካልመጣ አንችለውም ። ግን የሐራሬው ታዋቂ ስደተኛ እንዳለው አልጋ ሲሏቸው ቁንጫ የሞላበት መደብ የሚሉ አሉና የፖለቲካ ሰዎች ለፍተው ሊያስቁን ሲፍጨረጨሩ የማይገባቸው ጥቂት አይደሉም። መለስ ዜናዊ ከስልጣን ልወርድ ነኝ ብሎ ሲቀልድ በመሳቅ ፈንታ አምነውት ቁምጭጭ ያሉ ብዙ ናቸው። ይኸው ዓይን አውጣ ያለኝ ሀብት መፅሀፍት ብቻ ናቸውና ቤተ መፃህፍት ለማቋቋም ሰዎች ገንዘብ ከረዱኝ ብቻ ነው የምችለው ብሎ ሲኮምክ ቀልዱ አልገባ ብሏቸው የለም ገንዘብ አለህ፤ ከረሀብተኛ ሳይቀር ዘርፈሃል ብለው ሊከራከሩት የተነሱትንም አይተናል። ምርጫ ብሎ ሲሳለቅ አምነውት ምርጫ ሊወዳደሩ እንደሚነሱት ማለት ነው--በመሳቅ ፈንታ።

የፖለቲካ መሪዎቸ ሲቀልዱ ካልሳቅን ይበሳጫሉ፤ሲበሳጩ ደግሞ ብዙ ተጨማሪ ሰው ያጠቃሉ። እንሳቅላቸው፤ እንሳቅባቸው አደራ!